የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፴፪ኛ ዓመት ቁጥር ፴፱
አዲስ አበባ ሐምሌ ፫ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32th Year No. 39
ADDIS ABABA, 10th July, 2026

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፭፻፺፪/፪ሺ፲፰

በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው አካላት ተጠቃሚ የሚሆኑ ባለቤቶች መረጃ ግልጸኝነት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ……………….…..…ገጽ ፲፱ሺ፯፻፹፭

Content

Regulation No. 592/2026

Transparency of Legal Persons Beneficial Ownership Information Council of Ministers Regulation……...…...Page 19785

ደንብ ቁጥር ፭፻፺፪/፪ሺ፲፰

<u>በሕግ የሰውነት መብት ከተሰጣቸው አካላት ተጠቃሚ የሚሆኑ ባለቤቶችን መረጃ ግልጸኝነት ለመደንገግ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብንና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀሎችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ ቁጥር ፯፻፹/፪ሺ፭ (በአዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፹፯/፪ሺ፲፯ እንደተሻሻለው) አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

REGULATION No. 592/2026

COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE TRANSPARENCY OF LEGAL PERSONS' BENEFICIAL OWNERSHIP INFORMATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 55 Sub Article (1) of the Prevention and Suppression of Money Laundering and Financing of Terrorism Proclamation No. 780/2013 (as amended by Proclamation No. 1387/2025).

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው አካላት ተጠቃሚ የሚሆኑ ባለቤቶች መረጃ ግልጸኝነት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፭፻፺፪/፪ሺ፲፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. ትርጓሜ

የቃሉ ወይም የኃረጉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩/ **"ተጠቃሚ የሆነ ባለቤት"** ማለት በአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፲፰) ስር የተሰጠውን ትርጓሜ ይይዛል፤

፪/ **"መረጃ"** ማለት በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ተጠቃሚ የሆነ ባለቤት መረጃ ነው፤

፫/ **"በቂ መረጃ"** ማለት ተጠቃሚ የሆነ ባለቤትን እና ቁጥጥር የሚደረግባቸውን መንገዶች እና ዘዴዎች ለመለየት የሚያስችል መረጃ ነው፤

፬/ **"ትክክለኛ መረጃ"** ማለት ከገለልተኛ ምንጭ የተገኙ ሰነዶችን፣ ዳታ ወይም መረጃዎችን በመጠቀም ተጠቃሚ የሆነውን ባለቤት ማንነት እና ሁኔታ ለመለየት የሚረዳ እውነተኛነቱ የተረጋገጠ መረጃ ነው፤

PART ONE

GENERAL PROVISIONS

1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Transparency of Legal Persons" Beneficial Ownership Information Regulation No. 592/2026".

2. Definition

Unless the context requires otherwise, in this Regulation:

1/ **"Beneficial Owner"** means a definition stipulated under Article 2 Sub Article (18) of the Proclamation;

2/ **"Information"** means Beneficial Ownership Information of a legal person;

3/ **"Adequate Information"** means information that is sufficient to identify the natural person who is the beneficial owner and the means and mechanisms through which they exercise beneficial ownership or control;

4/ **"Accurate Information"** means information, which has been verified to confirm its accuracy by verifying the identity and status of the beneficial owner using reliable, independently sourced/obtained documents, data or information;

፭/ **“ህጋዊ ጥቅም”** ማለት ተጠቃሚ የሆነው ባለቤት መረጃን ለማግኘት በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብን ወይም ንብረትን ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን፤ ሽብርተኝነትንና የጅምላ ጨራሽ መሳሪያዎች ብዜትን በገንዘብ የመደገፍ ወንጀሎችን ለመከላከልና ለመዋጋት ፍላጎት እንዳለን የሚያሳይ በማስረጃ የተደገፈ መረጃ ለማግኘት የሚያስችል የተወሰነ፣ ትክክለኛ ምክንያት ነው፤

5/ **“Legitimate Interest”** means a specific, valid reason for needing to access the Information that is supported with evidence that can demonstrate an interest in the prevention of money laundering, its predicate offences, terrorist financing and the financing of proliferation of weapons of mass destruction;

፮/ **“ሚኒስቴር”** ማለት የኢፌዲሪ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ነው፤

6/ **“Ministry”** means the Ministry of Trade and Regional Integration of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

፯/ **“የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል”** ማለት በመንግሥት እና የግል አጋርነት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፸፮/፪ሺ፲ አንቀጽ ፲ መሰረት የተቋቋመ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ነው፤

7/ **“PPP Directorate General”** means a department established under Article 10 of Public Private Partnership Proclamation No. 1076/2018;

፰/ **“የመንግሥት እና የግል አጋርነት ቦርድ”** ማለት በመንግሥት እና የግል አጋርነት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፸፮/፪ሺ፲ አንቀጽ ፰ መሰረት የተቋቋመ ቦርድ ነው፤

8/ **“Public Private Partnership Board”** means a board established under article 8 of Public Private Partnership Proclamation No. 1076/2018;

፱/ **“የመንግሥት እና የግል አጋርነት”** ማለት በመንግሥት እና የግል አጋርነት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፸፮/፪ሺ፲ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፲፪) ስር ትርጓሜ የተሰጠው አጋርነት ነው፤

9/ **“Public Private Partnership”** means a partnership as defined under article 2 Sub Article (12) of Public Private Partnership Proclamation No. 1076/2018;

፲/ **“ማእከላዊ የመረጃ ጽሕፈት ቤት”** ማለት ተጠቃሚ የሆነ ባለቤትን መረጃ ለመመዝገብ በሚኒስቴሩ ስር የተደራጀ የመረጃ ማዕከል ነው፤

10/ **“Central Registry”** means a Beneficial Ownership Information Registry that is established under the Ministry;

፲፩/ **"ከፍተኛ አመራር"** ማለት በየግል ተቋማቱ የየራሱ ትርጓሜ የሚኖረው ሌላ ማንኛውንም ባለስልጣን ጨምሮ ለተቋሙ የዕለት ተዕለት ተግባር እንቅስቃሴ ስራ ሃላፊነት ያለበትን ሚኒስትር፣ ሚኒስትር ዴኤታ፣ ዋና ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ ከፍተኛ የሥራ አስፈጻሚ፣ ዳይሬክተር፣ ሥራ አስኪያጅ፣ ሴክሬታሪያት እና የመሳሰሉትን ያካትታል፤

፲፪/ **"አዋጅ"** ማለት በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብንና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር ፯፻፹/፪ሺ፭ (በአዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፹፯/፪ሺ፲፯ እንደተሻሻለው) ነው፤

፲፫/ በአዋጁ አንቀጽ ፪ ስር የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ተፈጻሚ ይሆናሉ፤

፲፬/ **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፭/ በደንቡ በወንድ ጾታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል።

፫. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

፩/ ይህ ደንብ በኢትዮጵያ ውስጥ በተመዘገቡ እና በሚንቀሳቀሱ በህግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው አካላት እንዲሁም የእነዚህ አካላት ተጠቃሚዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ደንቡ በሚከተሉት በህግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው አካላት ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡-

11/ **"Senior Manager"** means minister, state minister, general director, chief executive officer, senior executive officer, manager, secretariat, and any other official, as may be defined by individual institution, responsible for the running of day-to day business activities of the Legal person;

12/ **"Proclamation"** means the Prevention and Suppression of Money Laundering and Financing of Terrorism Proclamation No. 780/2013 (as amended by Proclamation No. 1387/2025);

13/ Words and phrases defined under Article 2 of the Proclamation shall be applicable to this Regulation;

14/ "**Person**" means any natural or legal person;

15/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

3. <u>Scope of Application</u>

1/ This Regulation shall be applicable on all legal persons registered and operate in Ethiopia, including the user of such legal person.

2/ Notwithstanding the provision of Sub Article (1) of this Article, the following legal persons are exempted from the application of this Regulation:

ሀ) በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣

ለ) በክልል ወይም በፌደራል መንግስት ሙሉ ለሙሉ በባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች፣

ሐ) በህብረት ስራ ማህበራት፣

መ) በመንግስት ተቋማት፣

ሠ) በሐይማኖት ተቋማት፣

ረ) በፖለቲካ ፓርቲዎች፣ እና

ሰ) ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸው ዓለም አቀፍ ተቋማት፡፡

a) civil Society Organizations;

b) enterprises wholly owned by Federal or Regional Governments;

c) cooperative associations;

d) public administrative organizations;

e) religious institutions;

f) political parties; and

g) international Organizations to which Ethiopia is a member.

ክፍል ሁለት
ተጠቃሚ የሆኑ ባለቤቶችን ስለመለየት እና ስለማሳወቅ
ንዑስ ክፍል አንድ
ተጠቃሚ የሆኑ ባለቤቶችን ስለመለየት

PART TWO
IDENTIFICATION AND DISCLOSURE OF BENEFICIAL OWNERS
SECTION ONE
IDENTIFICATION OF BENEFICIAL OWNERS

፬. መርህ

አግባብነት ያላቸው ሌሎች ህጎች እንደተጠበቁ ሆነው ለዚህ ደንብ ዓላማ የእያንዳንዱ በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ተጠቃሚ የሆነ ባለቤት ልዩ መለያ መገለጫዎች ከአንቀጽ ፭ እስከ አንቀጽ ፲፫ የተዘረዘሩት ናቸው፡፡

4. Principle

Without prejudice to other relevant laws, for the purpose of this Regulation, the specific identifying elements of a beneficial owner of each legal person are as provided under Article 5 to 13 of this Regulation.

፭. የአክስዮን ማህበር

፩/ ከሚከተሉት መስፈርቶች ውስጥ አንዱን ወይም ከዚያ በላይ የሚያሟላ የባለቤትነት ጥቅም ያለው ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው የአክስዮን ማህበር ተጠቃሚ የሆነ ባለቤት እንደሆነ ይቆጠራል፡-

5. Share Company

1/ A natural person with ownership interest who fulfils one or more of the following requirements shall be considered as a beneficial owner of a share company:

ሀ) በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ፤ በግልም ሆነ በጋራ፤ የአክሲዮን ማህበሩን ፲ (አስር) በመቶ ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የአክሲዮን ድርሻ በባለቤትነት የያዘ፤

ለ) ቅድሚያ የማግኘት መብት የሚያሰጥ አክስዮን የያዘ፤

ሐ) ከአክስዮን ማህበሩ አጠቃላይ ካፒታል ፲ (አስር) በመቶ ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ተለዋጭ የዕዳ ሰነድ የያዘ፡፡

፪/ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጨምሮ በሌሎች መንገዶች በአክስዮን ማህበሩ ላይ ቁጥጥር የሚያደርግ የተፈጥሮ ሰው፡-

ሀ) ማናቸውንም ዳይሬክተር፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ፣ ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ ሥራ አስኪያጅ ወይም ተመጣጣኝ ደረጃ ያለው ማንኛውንም ግለሰብ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የመሾም ወይም የመሻር መብት ያለው፤

ለ) የባለቤትነት ጥቅም ያለውን ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው በስጋና በጋብቻ ዝምድና፣ በሙያ፣ በንግድ፣ በስራ ወይም በሌላ በማናቸውም ተዋረዳዊ ወይም በማናቸውም ተገቢ ባልሆነ ተጽእኖዊ ግንኙነቶች ምክንያት በሌላ ሰው ቁጥጥር ስር ሆኖ የሚመራ ከሆነ፣

a) owns or holds, whether directly or indirectly, individually or jointly, 10 (Ten) percent or more shares of the Share Company;

b) holds a preferential share;

c) hold a convertible equity debt that amount to 10 (ten) percent or more of the total capital of the share company.

2/ A natural person who exerts control over a share Company through the following and other means:

a) having a right to, directly or indirectly, appoint or remove any Director, board of directors, Chief Executive Officer, manager or any individual with an equivalent status;

b) where the person with ownership interest is influenced or controlled by another person because of either an affinal, conjugal, professional, business, employment or any hierarchical or any undue influential relationships;

ሐ) በአክስዮን ማህበሩ ውስጥ የባለቤትነት ድርሻ ሳይኖር ማህበሩን በፋይናንስ በመደገፍ ውስጥ በመሳተፍ፣ ወይም በታሪካዊ ወይም ከውል በመነጨ ግንኙነት ምክንያት፣ ወይም አክስዮን ማህበሩ እዳዎች ላይ ክፍያዎች መፈጸም ባለመቻሉ የሚመነጭ ቁጥጥር፤

መ) የአክሲዮን ማህበሩን የገንዘብ፣ የንብረት ወይም የኢንቨስትመንት ውሳኔዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የመምራት ወይም የመቃወም መብት ያለው፤

፫/ የአክሲዮን ማህበሩን የንግድ አሠራር ወይም አጠቃላይ አቅጣጫ በመሠረታዊነት የሚነኩ ስልታዊ ውሳኔዎችን የመስጠት ኃላፊነት ያለው የተፈጥሮ ሰው እንዲሁም ዳይሬክተሮች፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ፣ ሥራ አስኪያጆች፣ ዋና የፋይናንስ ኦፊሰር፣ የተቆጣጣሪ ቦርድ አባላት፣ ሂሳብ አጣሪዎችን፣ ኦዲተሮች እና የማህበሩ ጸሀፊን ጨምሮ የማህበሩን የዕለት ተዕለት ወይም መደበኛ ጉዳዮች በከፍተኛ የአመራር ቦታ ላይ በመሆን የአስፈፃሚነት ቁጥጥር የሚያደርግ ግለሰብ፤

c) control without ownership by participating in the financing of the share Company, or because of historical or contractual associations, or if a share company defaults on certain payments;

d) having the right to, directly or indirectly, direct or veto the distribution of funds, assets, or investment decisions of the share company;

3/ A natural person responsible for strategic decisions that fundamentally affect the business practices or general direction of the share company as well as natural person who exercises executive control over the daily or regular affairs of the share Company through a chairperson of the board of directors, board directors, managers, chief finance officer, board members of internal control, Liquidators and Auditors;

፬/ በማዕድን ዘርፍ፣ በሪል ስቴት ልማት፣ በባለሞተር ተሽከርካሪ ነጋዴነት፣ አስመጪና ላኪ ዘርፍ ወይም ሌሎች ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የሚወሰኑ ዘርፎችን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በግል ወይም በጋራ ፭ (አምስት) በመቶ ወይም ከዚያ በላይ የአክሲዮን ባለቤት የሆነ ግለሰብ፡፡

፮. ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር

፩/ አክሲዮኖችን ወይም ድምጽ የመስጠት መብቶችን ጨምሮ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ፤ በግልም ሆነ በጋራ፤ ፭ (አምስት) በመቶ ወይም ከዚያ በላይ የማህበሩ ድርሻ ባለቤት የሆነ ማንኛውም ግለሰብ የማህበሩ ተጠቃሚ የሆነ ባለቤት እንደሆነ ይቆጠራል።

፪/ የዚህ ደንብ አንቀፅ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) ድንጋጌዎች እንደ አግባብነታቸው ለኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበርም ተፈጻሚ ይሆናሉ።

፯. ባለ አንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር

፩/ ማህበሩን በባለቤትነት የያዘው ግለሰብ እና ብቸኛ አባል ያልሆነ ዋና ሥራ አስኪያጅ የማህበሩ ተጠቃሚ የሆነ ባለቤት እንደሆነ ይቆጠራል።

፪/ የዚህ ደንብ አንቀፅ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) ድንጋጌዎች እንደ አግባብነታቸው ለባለ አንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበርም ተፈጻሚ ይሆናሉ።

4/ A natural person who owns or holds, directly or indirectly, individually or jointly, 5 (Five) percent or more of share in a Share company that are engaged in mining, Real estate development, motor vehicle dealership, Import and export sectors or other sectors that will be determined by a Directive, shall be considered as a beneficial owner of the share Company.

6. Private Limited Company

1/ Any natural person who owns or holds, whether directly or indirectly, individually or jointly, 5 (Five) percent or more shares of the Private Limited Company shall be considered as the Beneficial Owner.

2/ Sub Article (2) and (3) of Article 5 of this Regulation shall be applicable to the Private limited company as appropriate.

7. One Member Private Limited Company

1/ A natural person who owns the company and general manager who is not a sole member of the company shall be considered as the Beneficial Owner.

2/ Sub Article (2) and (3) of Article 5 of this Regulation shall be applicable to the one man private limited company as appropriate.

፰. **የኅብረት ሽርክና ማህበር**

፩/ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በጋራም ሆነ በግል በትርፍ ወይም ማህበሩ በሚፈርስበት ጊዜ በንብረት ክፍፍል ላይ ወይም ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ ፳፭ በመቶ ወይም ከዚያ በላይ ድርሻ ወይም ድምጽ የመስጠት መብት ያለው ማንኛውም ግለሰብ የማህበሩ ተጠቃሚ የሆነ ባለቤት እንደሆነ ይቆጠራል።

፪/ የሽርክና ማህበሩ ፳፭ በመቶ ወይም ከዚያ በላይ የሚሆን ትርፍ ወይም ንብረት ከድርሻ የሚገኝ ጥቅምና መብት የተላለፈለት ማንኛውም ሶስተኛ ወገን የሆነ ግለሰብ የማህበሩ ተጠቃሚ የሆነ ባለቤት እንደሆነ ይቆጠራል።

፫/ የዚህ ደንብ አንቀፅ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) ድንጋጌዎች እንደ አግባብነታቸው ለህብረት ሽርክና ማኅበርም ተፈጻሚ ይሆናሉ።

፱. **ሁለት ዓይነት ኃላፊነት ያለበት የሽርክና ማኅበር**

፩/ በትርፍ ወይም ማህበሩ በሚፈርስበት ጊዜ በንብረት ክፍፍል ወይም በውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሽርክና ማህበሩ ፳፭ በመቶ ወይም ከዚያ በላይ ድርሻ ያለው ማንኛውም ኃላፊነቱ ያልተወሰነ ሽሪክ እና ኃላፊነቱ የተወሰነ ሽሪክ የማህበሩ ተጠቃሚ የሆነ ባለቤት እንደሆነ ይቆጠራል።

፪/ የዚህ ደንብ አንቀፅ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) ድንጋጌዎች እንደ አግባብነታቸው ሁለት ዓይነት ኃላፊነት ላለበት የሽርክና ማኅበርም ተፈጻሚ ይሆናሉ።

8. **General partnership**

1/ Any natural person who Directly or indirectly, jointly or individually, holds 25 (Twenty Five) percent or more share on the distribution of profit or asset in time of dissolution of the General Partnership or voting right on decision making shall be considered as a beneficial owner.

2/ A third party natural person in which a beneficial interests and rights in the share of a partner is transferred to where such beneficial interest and rights are 25 (Twenty Five) percent or more of the profit or asset of the partnership shall be considered as a beneficial owner.

3/ Sub Article (2) and (3) of Article 5 of this Regulation shall be applicable to the General partnership as appropriate.

9. **Limited Partnership**

1/ General Partners and Limited partners with 25 (Twenty Five) percent or more share on the distribution of profit or asset in time of dissolution of the Limited Partnership or voting right on decision making shall be considered as a beneficial owner.

2/ Sub Article (2) and (3) of Article 5 of this Regulation shall be applicable to the limited partnership as appropriate.

፲. ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማህበር

፩/ የሽርክና ማህበሩ በትርፍ ወይም በሚፈርስበት ጊዜ የንብረት ክፍፍል ላይ ፳፭ በመቶ ወይም ከዚያ በላይ ድርሻ ያለው ሽሪክ የማህበሩ ተጠቃሚ የሆነ ባለቤት እንደሆነ ይቆጠራል።

፪/ የዚህ ደንብ አንቀፅ ፭ ንኡስ አንቀጽ (፪) እና (፫) ድንጋጌዎች እንደ አግባብነታቸው ኃላፊነቱ ለተወሰነ የሽርክና ማኅበርም ተፈጻሚ ይሆናሉ።

10. Limited liability partnership

1/ A natural person Partners with 25 (twenty-five) percent or more share on the distribution of profit or asset in time of dissolution of the Partnership shall be considered as a beneficial owner.

2/ Sub Article (2) and (3) of Article 5 of this Regulation shall be applicable to the limited liability partnership as appropriate.

፲፩. በውጭ አገር ስለተቋቋመ በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል

፩/ ኢትዮጵያ ውስጥ ኢንቨስት ለማድረግ፣ የንግድ ስራ ለማከናወን ወይም የማይንቀሳቀስ ንብረትን በባለቤትነት ለመያዝ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ ማንኛውም በውጭ አገር በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ከመመዝገቡ በፊት ወይም በምዝገባ ላይ በቂ፣ ትክክለኛ እና ወቅታዊ የሆነ ተጠቃሚ የሆነ ባለቤት መረጃን ለሚኒስቴሩ ወይም ለሚመለከተው የመንግስት ተቋም ማቅረብ አለበት።

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሰረት የሚቀርበው ማንኛውም መረጃ ወይም ሰነድ ድርጅቱ በተቋቋመበት ሀገር አግባብ ባለው ባለስልጣን የተሰጠ ወይም የተረጋገጠ እና በኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ተረጋግጦ ከኦፊሴላዊ ሰነዶች ጋር አብሮ መቅረብ አለበት።

11. Foreign Established Legal Persons

1/ Every foreign legal person that registers, invests, conducts business activities or own an immovable property in Ethiopia, prior to or upon registration, shall submit adequate, accurate, and up-to-date beneficial ownership information to the Ministry or the relevant authority, and shall be authorized by the ministry of Ethiopian Foreign Affairs.

2/ Any information or document submitted pursuant to Sub Article (1) of this Article shall be accompanied with official documentation issued or attested by the competent authority of the legal person's home jurisdiction.

፫/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፪) እንደተጠበቀ ሆኖ በኢትዮጵያ ህግ እውቅና የተሰጣቸው የተመዘገቡ እና የተረጋገጡ ሰነዶች ለምዝገባ ሊቀርቡ ይችላሉ።

፲፪. የመንግስት የግል አጋርነት

፩/ ማንኛውም ፳፭ በመቶ ወይም ከዚያ በላይ የመንግስት የግል አጋርነት የሽርክና ወይም የንብረት ድርሻ በባለቤትነት በመያዝ በአጋርነቱ ውስጥ የተሰማራ ግለሰብ ነጋዴ ወይም ኢንቨስተር የአጋርነቱ ተጠቃሚ የሆነ ባለቤት እንደሆነ ይቆጠራል።

፪/ የዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው ለመንግሥትና የግል አጋርነትም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

፫/ በዚህ ደንብ መሠረት መረጃን ያስመዘገበ ማንኛውም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ለመንግስትና ለግል አጋርነት ዓላማ ሲባል ተጠቃሚ የሆነ ባለቤት መረጃን የማስመዝገብ ግዴታ የለበትም።

፬/ የመንግስት የግል አጋርነት ቦርድ እና የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል መረጃን የመሰብሰብ፣ የመያዝ እና ለሚኒስቴሩ ሪፖርት የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው።

3/ Without prejudice to Sub Article (2) of this Article, notarized and authenticated records recognized under Ethiopian law may be submitted to Registration.

12. Public Private Partnership

1/ Any natural person trader or investor, who engages in a Public Private Partnership arrangement, with 25 percent or more of the share or asset of the Partnership shall be considered as a Beneficial Owner of the partnership.

2/ Sub Article (2) and (3) of Article 5 of this Regulation shall be applicable to public private partnership as appropriate.

3/ Any legal person that has registered its Information under this Regulation shall not be obliged to report its beneficial owners for the purpose of the public private partnership arrangement.

4/ The Public Private Partnership Board and the PPP Directorate General shall obtain, hold and report information to the Ministry.

፲፫. የፋይናንስ ተቋም

፩/ ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ፣ በግልም ሆነ በጋራ፣ የፋይናንስ ተቋሙን ፪ (ሁለት) በመቶ ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የአክሲዮን ድርሻ ወይም ድምጽ የመስጠት መብት በባለቤትነት ከያዘ ወይም ከፋይናንስ ተቋሙ አጠቃላይ ካፒታል ፪ (ሁለት) በመቶ ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ተለዋጭ የዕዳ ሰነድ ከያዘ የፋይናንስ ተቋሙ ተጠቃሚ የሆነ ባለቤት እንደሆነ ይቆጠራል።

፪/ የዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ለ)፣ (፪) እና (፫) ድንጋጌዎች ለፋይናንስ ተቋማትም ተፈጻሚ ይሆናሉ።

ንዑስ ክፍል ሁለት
ተጠቃሚ የሚሆን ባለቤት መረጃን ስለማሳወቅ

፲፬. መረጃን የመሰብሰብ፣ የመያዝ እና ሪፖርት የማድረግ ግዴታ

፩/ ማንኛውም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል መረጃን:-

ሀ) የመሰብሰብ፣

ለ) በተማከለ መልኩ የመያዝ፣

ሐ) ለሚኒስቴሩ፣ ለገቢዎች ሚኒስቴር፣ ለፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና ሙያዎች ሪፖርት የማድረግ፣

13. Financial Institution

1/ Any natural person who owns or holds, whether directly or indirectly, individually or jointly, 2 (Two) percent or more shares of the Financial Institution or hold a convertible equity debt that amounts to 2 (Two) percent or more of the total capital of the Financial Institution shall be considered as a beneficial owner of the Financial Institution.

2/ Sub Articles (1) (b), (2) and (3) of Article 5 of this Regulation shall be applicable to the financial institutions as appropriate.

SECTION TWO
DISCLOSURE OF BENEFICIAL OWNERSHIP INFORMATION

14. Obligation to Obtain Hold and Report Information

1/ Any Legal person shall:

a) Collect Information;

b) Hold Information in a centralized manner;

c) Report the Information to the Ministry, the Ministry of Revenue, Financial Institutions and Designated Non-Financial Business and Professions;

መ) ለሚኒስቴሩ፣ አግባብነት ላለው ባለስልጣን፤ ለኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን፤ እና ለመንግስት የግዥ አገልግሎት እና ለፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና ሙያዎች ሲጠየቅ በ፵፰ ሰዓት ውስጥ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

፪/ በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተመላከተው መረጃ በቂ፣ ትክክለኛ እና ወቅታዊ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፫/ በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚሰበሰበውን መረጃ የሚደግፍ ሰነዶችን መቀበል አለበት፡፡

፲፭. <u>ተጠቃሚ የሆነ ባለቤት ዝርዝር መረጃዎች</u>

፩/ በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ተጠቃሚ የሆነ ባለቤት መረጃ የሚከተሉትን ዝርዝሮች መያዝ፣ መሰብሰብ፣ ሪፖርት ማድረግ እና መግለጽ አለበት፡-

ሀ) ሙሉ ስም፤

ለ) ጾታ፤

ሐ) የትውልድ ቀን፤

መ) የትውልድ ቦታ፤

ሠ) ዜግነት፤

ረ) የመኖሪያ አድራሻ፤

ሰ) የኢሜል አድራሻ፤

ሽ) የስልክ ቁጥሮች፤

ቀ) የስራ ሀላፊነት ወይም ሙያ፤

d) Disclose their Information to the Ministry, Competent Authorities, Ethiopian Capital Market Authority, and Public Procurement Service and co-operate with Financial Institutions and Designated Non-Financial Business and Professions, up on request, within 48 hours.

2/ The legal person shall ensure Information referred under Sub Article (1) of this Article are adequate, accurate and up-to-date.

3/ The legal person shall receive document to support the information gathered under Sub Article (1) of this Article.

15. <u>Particulars of Beneficial Ownership Information</u>

1/ A legal person shall obtain, maintain, report and disclose the following particulars of the natural person identified as a beneficial owner:

a) full name;

b) gender;

c) date of birth;

d) place of birth;

e) nationality;

f) residential address;

g) email address;

h) telephone number;

i) occupation or profession;

በ) የግለሰቡ ፋይዳ ዲጂታል መታወቂያ፣ ፓስፖርት፣ መንጃ ፍቃድ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የቀበሌ ዲጂታል መታወቂያ ወይም ሌሎች ከመንግስት የተሰጡ ግለሰቡን የሚለዩ ሰነዶች የሚከተሉትን ያካተቱ መሆን አለባቸው፡-

i) የመታወቂያ ቁጥር፣

ii) የተሰጠበት ሀገር፣ እና

iii) የተሰጠበት ቀን እና የሚያበቃበት ቀን።

ተ) ግለሰቡ በድርጅቱ ውስጥ ያለው የባለቤትነት ወይም የቁጥጥር ባህሪ፣ ዓይነት እና መጠን፤

ቸ) ግለሰቡ ተጠቃሚ የሆነ ባለቤት ሆኖ በድርጅቱ ውስጥ የተመዘገበበት ወይም ባለቤትነቱ ያበቃበት ቀን፤

ኀ) ግለሰቡ ለፖለቲካ ተፅእኖ የተጋለጠ ሰው መሆን አለመሆኑን፤ እና

ነ) ሚኒስቴሩ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚጠይቃቸውን ሌሎች አስፈላጊ ዝርዝሮች፡፡

፪/ በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተጠቀሱትን ዝርዝር መረጃዎች ቅጂ ለሚኒስቴሩ ከማቅረቡ በፊት ያረጋግጣል።

j) data from the individual’s Fayda Digital ID, valid passport, driver’s license, Tax Identification Number, Residential Kebele Digital ID or other government-issued document that identifies the individual including:

i) identification number;

ii) country of issue; and

iii) date of issue and of expiry.

k) nature, type and extent in which the individual owns or exercises control of the legal person;

l) the date on which the individual became or ceased to be a registrable beneficial owner in relation to the legal person in question;

m) whether the individual is a politically exposed person; and

n) any other relevant detail the Ministry may require from time to time.

2/ A legal person shall verify the particulars referred to in Sub Article (1) of this Article before submitting a copy of the particulars to the Ministry.

፫/ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተጠቀሱት ዝርዝሮች ላይ ለውጥ በሚያደርግበት ጊዜ ለውጦቹን በ ፲፬ ቀናት ውስጥ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ማድረግ አለበት።

፬/ በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ተጠቃሚ የሚሆነውን ባለቤት በንዑስ አንቀጽ (፩) ውስጥ የተጠቀሱትን ዝርዝሮች እንዲገመግም እና እንዲያረጋግጥ ሊጠይቅ ይችላል።

፲፮. የመረጃ ምዝገባ መኮንን ስለመመደብ

፩/ በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል በከፍተኛ አመራር ክትትል የሚደረግበት እና በዚህ ደንብ የተቀመጡ የህግ ግዴታዎችን የሚያስፈፅም የመረጃ ምዝገባ መኮንን መመደብ አለበት።

፪/ በህግ የሰውነት መብት በተሰጠው አካል የተመደበው የመረጃ ምዝገባ መኮንን መረጃውን ለሚኒስቴሩ እና ሌሎች በዚህ ደንብ መሰረት ለተፈቀደላቸው አካላት ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለበት።

3/ Pursuant to Sub Article (1) of this Article When there are any changes in the particulars of a legal person, such changes have to be reported to the Ministry within 14 days of the change.

4/ A legal person may request its beneficial owner to review and verify any of the beneficial owner's particulars referred under Sub Article (1) of this Article.

16. Assignment of Beneficial Ownership Information Registration Officer

1/ Legal persons shall appoint an information registration officer specifically responsible, under the legal person's Senior Management oversight to discharge the legal requirements stipulated by this Regulation.

2/ An information registration officer has an obligation to report the information to the Ministry and other authorized persons in this Regulation.

፲፯. ተጠቃሚ የሆነ ባለቤትን መረጃ በየጊዜው ስለመገምገም

፩/ የዚህ ደንብ አንቀፅ ፲፭ ንኡስ አንቀስ (፫) እንደተጠበቀ ሆኖ እያንዳንዱ በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ቢያንስ በአመት ሁለት ጊዜ ተጠቃሚ ከሆነው ባለቤት አስፈላጊ መረጃዎች ጋር የተያያዙ ማንኛውንም ለውጦች የመገምገም እና የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት።

፪/ በግምገማው ሂደት የተለዩ ማናቸውም መረጃዎች በ፲፬ ቀናት ውስጥ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት መደረግ አለባቸው።

፫/ ማንኛውም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል በየጊዜው የሚደረጉ ግምገማዎችን ሰነድ መያዝ እና የሚመለከተው ባለስልጣን እንዲያገኘው ዝግጁ ማድረግ አለበት።

፲፰. የመተባበር ግዴታ

በህግ የሰውነት መብት በተሰጠው አካል የተመደበ ማንኛውም የመረጃ ምዝገባ መኮንን፣ ከፍተኛ አመራር ወይም ተጠቃሚ የሆነው ባለቤት በሚኒስቴሩ በሚጠየቅበት ጊዜ በአካል የመቅረብ፣ መረጃና ማስረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

17. Periodic Review of Beneficial Owners Information

1/ Without any prejudice to Article 15 Sub Article (3) of this Regulation, every legal person shall, at least Twice in every calendar year, review and verify its beneficial owners and relevant information, including any changes required to be made to the registerable particulars of a beneficial owner.

2/ Any Information identified through the review shall be reported to the Ministry within 14 days.

3/ The legal person shall document the periodic review activities and made accessible to the concerned authority for consideration.

18. Obligation to Cooperate

Any information registration officer, a member of senior managers or beneficial owner of a legal person shall have an obligation to appear, provide information and evidence where requested by the Ministry.

፲፱. መረጃን ያለመግለጽ ውጤቶች

፩/ የሚፈለገው መረጃ በዚህ ደንብ እና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች ድንጋጌዎች መሰረት እስካልቀረበ፣ እስካልተረጋገጠ እና በሚኒስቴሩ እስካልተመዘገበ ድረስ ለማንኛውም በህግ የሰውነት መብት ለተሰጠው አካል የንግድ ምዝገባ፣ የንግድ ሥራ ፈቃድ ወይም የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሊሰጥ ወይም ሊታደስ አይችልም፡፡

፪/ መረጃውን መግለጽ ወይም ማረጋገጥ ያለመቻል በህግ የሰውነት መብት ለተሰጠው አካል ምዝገባ ለመከልከል እና የኢንቨስትመንት ወይም ሌላ ፈቃድ ለማገድ ወይም ለመሰረዝ በቂ ምክንያት ይሆናል።

፫/ መረጃዎችን ያለመግለጽ ተጠያቂነት በዚህ ደንብ መሰረት መረጃን እና በመረጃው ላይ የሚደረጉ ለውጦችን የማሰባሰብ፣ የማስቀመጥ፣ በወቅቱ ሪፖርት የማድረግ እና በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ግዴታዎቹን እየተወጣ ስለመሆኑ የመከታተል ግዴታ በተጣለባቸው ኦፊሰሮችና ከፍተኛ ሀላፊዎች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

19. Effects of Non Disclosure

1/ No commercial registration, business license, or investment permit, nor any renewal thereof, shall be issued to any legal person unless the required Information has been duly submitted, , verified, and recorded by the Ministry, in accordance with this Regulation and other relevant laws.

2/ Failure by the legal person to disclose such information shall constitute sufficient ground for refusal, suspension, or revocation of the legal person's trade registration, business license, or investment permit.

3/ The liability of non disclosure may be extended to Officers and senior managers who have an obligation to collect, hold and report Information, and its updates, in a timely manner, and oversight the execution of the obligations by the legal person, under this Regulation.

ክፍል ሦስት

ስለ ተቆጣጣሪ አካላት ሥልጣንና ተግባር እና ስለ ተጠቃሚ የሆነ ባለቤት መረጃ ምዝገባ

፳. የሚኒስቴሩ ስልጣንና ተግባር

በሌሎች ሕጎች የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩/ የዚህን ደንብ አፈጻጸም የሚቆጣጠር ማእከላዊ የመረጃ ጽሕፈት ቤት የማደራጀትና የአሰራር ስርዓት የመዘርጋት፤

፪/ በዚህ ደንብ መሰረት መረጃ የመሰብሰብ፣ የማደራጀት፣ የማረጋገጥ እና የመያዝ፤

፫/ በህግ የሰውነት መብት የተሰጠውን አካል ማንኛውንም መረጃ የመጠየቅና የመድረስ እንዲሁም የመረጃ ምዝገባ መኮንን፣ ከፍተኛ ኃላፊን ወይም ተጠቃሚ የሆነ ባለቤትን የመጥራት እና መረጃ ወይም ማስረጃ የመጠየቅ፤

፬/ በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል የሚጠይቀው እያንዳንዱ አዲስ የንግድ ምዝገባና የንግድ ሥራ ፈቃድ በዚህ ደንብ መሠረት ተገቢውን መረጃ አካቶ መቅረቡን የማረጋገጥ፤

፭/ መረጃ በቂ፣ ትክክለኛ፣ የተሟላ እና ወቅታዊ መሆኑን የማረጋገጥ፤

፮/ የዳታ ሚስጢራዊነት እና ምሉዕነት እንዲጠበቅ የማድረግ፤

PART THREE

POWERS AND DUTIES OF REGULATORY BODIES AND BENEFICIAL OWNERSHIP INFORMATION REGISTRATION

20. Powers and Duties of the Ministry

Without prejudice to powers and duties given in other relevant laws, the Ministry shall have the following powers and responsibilities:

1/ Organize a central registry office and establish its working procedure to oversee the implementation of this Regulation;

2/ Collect, verify, and store Information as required under this Regulation;

3/ Request and access any information from the legal person and summon any information registration Officer, senior managers or Beneficial owners to provide information and evidence;

4/ Make sure every new commercial registration and business licensing of legal persons be accompanied with a reporting of Information in accordance with this Regulation;

5/ Ensure the adequacy, accuracy, completeness and updatedness of the information;

6/ Implement necessary measures to protect the confidentiality and integrity of the data;

፯/ የመረጃ ተደራሽነት ፈቃድ የመስጠትና የመሰረዝ፤

፰/ አግባብነት ላለው ባለስልጣን፣ ለፋይናንስ ተቋም፣ ፋይናንስ ነክ ላልሆነ የተሰየመ የንግድና የሙያ ሥራ ባለቤት እንዲሁም ለሌላ ሀገር አግባብነት ያለው አካል የመረጃ ተደራሽነትን የማመቻቸት፤

፱/ ለመረጃ ግልፀኝነት ህግ ተገዢ የሆነ በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል አስቀድሞ እንዲያውቀው በማድረግ ወይም ሳያሳውቅ ቁጥጥርና ምርመራ የማድረግ፤

፲/ በዚህ ደንብ መሰረት ግዴታውን ባለመወጣት ጥፋት በፈጸመ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት በተሰጠው አካል ላይ አስተዳደራዊ ቅጣት የመጣል፤

፲፩/ አግባብነት ላለው ባለስልጣን፣ የፋይናንስ ተቋም፣ ፋይናንስ ነክ ላልሆነ የተሰየመ የንግድና የሙያ ሥራ ባለቤት እና ለሌላ ህጋዊ ጥቅም ላለው ሰው የመረጃ ተደራሽነት አሰራር፣ ሁኔታ እና የተደራሽነት ክፍያ የመወሰን፤

፲፪/ ህጋዊ በሆነ አግባብ የሚቀርብለትን ቅሬታ ተቀብሎ ውሳኔ የመስጠት፤

፲፫/ ይህንን ደንብ ለማስፈጸም ከፌደራል መንግስት፣ ከክልልና የከተማ አስተዳደር ተቋማት ጋር በትብብር የመሥራት፡፡

7/ Grant or revoke access to the Registry;

8/ Facilitate access to the Registry for competent authorities, Financial Institutions, Designated non-financial Business and Professions and other countries' competent authorities, in a timely manner;

9/ Monitor and inspect with or without notifying the legal persons who are subject to Information transparency laws;

10/ Impose administrative sanction on legal persons, natural persons who are found to be in default of implementing the obligations stipulated under this Regulation;

11/ Set terms, conditions and access fee to facilitate timely access the Registry by Financial institutions, Designated non-financial Business and Professions and other persons with legitimate interest;

12/ Receive and determine on the complaints submitted by individual with a legitimate grievance;

13/ Cooperate and coordinate with Federal Government, and regional and City administration authorities on the implementation of this Regulation.

፳፩. የክልልና የከተማ መስተዳደር የንግድ ቢሮ ሥልጣንና ተግባር

በሌሎች ሕጎች የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው የክልልና የከተማ መስተዳደር የንግድ ቢሮ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩/ የንግድ ፈቃድ፣ ምዝገባ ወይም አገልግሎት ከሚጠይቀው በህግ የሰውነት መብት ከተሰጠው አካል መረጃን የመቀበልና የመያዝ፤

፪/ ሚኒስቴሩን በመረጃ አሰባሰብ፣ ምዝገባ እና ማረጋገጥ ሂደት የማገዝ፤

፫/ ማንኛውንም የመረጃ መጣረስ ወይም ያልተገባ መረጃ ለሚኒስቴሩ ወዲያውኑ የማሳወቅ፤

፬/ ከሚኒስቴሩ እና ከሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማት ጋር በትብብር የመስራት፡፡

፳፪. የገቢዎች ሚኒስቴር ስልጣንና ተግባር

በሌሎች ሕጎች የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው የገቢዎች ሚኒስቴር የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩/ ማንኛውም በኢትዮጵያ ውስጥ ለግብር አስተዳደር ህግ ተገዢ የሆነን በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል መረጃ የማሰባሰብ፣ የማረጋገጥና የመያዝ፤

21. Powers and Duties of the Regional and City Administration Trade Bureaus

Without prejudice to powers and duties given in other relevant laws, the Regional and city administration trade bureaus shall have the following powers and responsibilities:

1/ Obtain and hold information from legal persons that they register or provide business license;

2/ Assist the Ministry in the collection, registration and verification of Information;

3/ Report any discrepancies or irregularities in beneficial ownership information to the Ministry promptly;

4/ Work in coordination with the Ministry and other relevant government authorities.

22. Powers and Duties of the Ministry of Revenues

Without prejudice to powers and duties given in other relevant laws, the Ministry of Revenue shall have the following powers and responsibilities:

1/ Obtain, verify, and hold adequate, accurate, and updated Information of Legal Persons subject for any tax administration in Ethiopia;

፪/ መረጃው በቂ፣ ትክክለኛና ወቅታዊ መሆኑን ለማረጋገጥ አስፈላጊ ተግባራትን የመፈጸም፤ በማንኛውም ጊዜ በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል፣ የፋይናንስ ተቋም፣ ፋይናንስ ነክ ያልሆነ የተሰየመ የንግድና የሙያ ስራ ባለቤት ወይም ሚኒስቴሩ መረጃ እንዲያቀርብ፣ እንዲያረጋግጥ ወይም ወቅታዊ እንዲያደርግ የመጠየቅ፤

፫/ በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች መሰረት የሚገኝ መረጃ በዋነኝነት ለግብር አወሳሰን፣ አሰባሰብና አፈጻጸም እንዲሁም የግብር ስወራን እና መሸሽን ለመከላከል ዓላማ እንዲውል የማድረግ፤

፬/ ከሚኒስቴሩ እና ከሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማት ጋር በትብብር የመስራት፡፡

፳፫. <u>የክልልና የከተማ መስተዳደር የገቢዎች ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት</u>

በሌሎች ሕጎች የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው የክልልና የከተማ መስተዳደር የገቢዎች ቢሮ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፪ የተመለከቱትን ተግባርና ኃላፊነቶች በክልሉ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

2/ Take all necessary measures to ensure the information is adequate, accurate and up-to-date; Require, at any time, a Legal person, Financial Institution, Designated non-financial Business and Professions or the Registry to provide, confirm or update its Information;

3/ Use Information obtained under this section primarily for the purposes of the assessment, collection, and enforcement of taxes, and for the prevention of tax evasion and avoidance;

4/ Work in coordination with the Ministry and other relevant government authorities.

23. <u>Powers and Resiponsibilities of the Regional and City Administration Revenue Bureaus</u>

Without prejudice to the powers and responsibilities given in other laws, the Regional and City Administration Revenue Bureau shall exercise the powers and responsibilities provided under Article 22 of this Regulation in the region.

፳፬. የፌዴራል መንግስት የግዢ አገልግሎት ስልጣንና ተግባር

፩/ በሌሎች ሕጎች የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው የፌደራል መንግሥት የግዥ አገልግሎት የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) በሚኒስቴሩ ለሚያዝ መረጃ በቀጥታ ተደራሽ የመሆን፤

ለ) በመንግስት የግዢ ሂደት ውስጥ ከተሳተፈ በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል መረጃ የመሰብሰብ፤

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (ለ) መሰረት ያገኘውን መረጃ በሚኒስቴሩ ከተያዘው መረጃ ጋር መናበቡን የማረጋገጥ፤

መ) በመረጃ ማሰባሰብ ሂደት የተለየ የመረጃ መጣረስ በሚመለከተው በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል በ፭ (አምስት) የስራ ቀናት ውስጥ እንዲታረም የማድረግ፤

ሠ) መረጃውን ያላስገባ ወይም ያላረመ ማንኛውም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል በማንኛውም የመንግስት ግዢ ሂደት እንዳይሳተፍ የማገድ።

፪/ በዚህ ደንብ መሰረት ማንኛውም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ጋር በግዢ የተሳተፈ ማንኛውም የመንግስት ተቋም የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆኑበታል።

24. Powers and Duties of the Federal Public Procurement Service

1/ Without prejudice to powers and duties given in other relevant laws, the Federal Public Procurement Service shall have the following powers and responsibilities:

a) have direct access to Information held by the Ministry;

b) request Information from a legal person who participate in public procurement activities;

c) cross-check and ensure that the Information obtained pursuant to Sub Article (b) hereinabove is verified against Information held by the Ministry;

d) rectify Discrepancies found in due process by the concerned legal person with in 5 (Five) working days;

e) cause the suspension of any legal person in the engagement of public procurement that fails to rectify discrepancies on its Information.

2/ The provisions of this article shall be applicable to government authorities who enter in a procurement activity with legal persons covered under this Regulation.

፫/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች በክልል መንግስት እና በከተማ አስተዳደሮች ላይ ተፈጻሚነት አላቸው።

፳፭. ስለመረጃ አያያዝ

፩/ ሚኒስቴሩ ቅልጥፍና፣ ዋስትና እና ቀላል ተደራሽነትን በሚያረጋግጥ ሁኔታ መረጃን በሰነድ፤ በመግነጢሳዊ፣ በኤሌክትሮኒክ ወይም በሌላ የአያያዝ ዘዴ መያዝ አለበት።

፪/ የመረጃ አያያዝ ስርዓቱ ከማንኛውም ያልተፈቀደ ተደራሽነት የሚጠብቅ፤ መልሶ የማግኘት እና ምትክ ቅጂ የሚይዝ ስርዓትን ያቀፈ መሆን አለበት።

፫/ ሚኒስቴሩ የሚከተሉትን መረጃዎች ጨምሮ የተሟላ መዝገብ መያዝ አለበት፡-

ሀ) ገቢ የተደረገ መረጃ ዋና ቅጂ፤

ለ) ማንኛውንም የመረጃ ማሻሻያ እና ማስተካከያ፤

ሐ) ማንኛውንም የሕግ ተገዢነት፣ የምርመራ፣ ተደራሽ የሆነና የተጋራ መረጃ፤

መ) ከሌላ ሀገር መሰል የሆነ አግባብነት ያለው ባለስልጣን የተጠየቀ ወይም ገቢ የተደረገ መረጃ እና የተሰጠ ወይም ገቢ የተደረገ መልስ።

፬/ የዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፬ ንዑስ አንቀጽ (፬) በመዝገብ አያያዙ ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

3/ The provisions of this Article shall be applicable to Regional governments and City administrations.

25. Maintenance of Information

1/ The Ministry shall maintain Information in manually, magnetic, electronic or other data storage form to ensure efficiency, security, and ease of access.

2/ The system shall include features for data backup, recovery, and protection against unauthorized access.

3/ The Ministry shall maintain comprehensive records of all Information, including:

a) original submissions of the Information;

b) any amendments or updates to the information;

c) records of compliance, inspections, access and sharing to the Registry;

d) information requested by and submitted to and responses given to or obtained from foreign counter competent authorities.

4/ Sub Article (4) of Article 14 of this Regulation shall be applicable to the Registry.

፳፮. መረጃን ስለማስወገድ ወይም ስለማሻሻል

፩/ ሚኒስቴሩ በሚከተሉት ሁኔታዎች መሰረት መረጃን ለማስወገድ ወይም ለማሻሻል ስልጣን ይኖረዋል፦

ሀ) ተገቢው ሰነድ መቅረቡ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ወይም ተጠቃሚ በሆነው ባለቤት ጠያቂነት፤

ለ) የማረጋገጥ ስራ ከተሰራ በኋላ መረጃው ትክክል ያልሆነ ወይም አሳሳች ሆኖ ሲገኝ፤

ሐ) ህጋዊ ጥቅም ባላቸው ሰዎች በሚቀርብ ቅሬታ መሰረት፤

መ) አግባብነት ባለው ፍርድ ቤት በሚሰጥ ውሳኔ መሰረት፤

ሠ) አስፈላጊውን መረጃ በማስገባት ሂደት ተለይቶ በታወቀ ስህተት መነሻነት፤

ረ) በማንኛውም አስቀድሞ ባልታወቀ እና የመረጃውን መሻሻል በሚፈልግ ጉዳይ።

፪/ ሚኒስቴሩ መረጃውን ከማሻሻሉ በፊት የሚመለከተውን በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ስህተቱን እንዲያርም መጠየቅ አለበት።

፫/ ሚኒስቴሩ እያንዳንዱን የተሻሻለ እና የተወገደ መረጃን ከነ ምክንያቱ መዝግቦ መያዝ አለበት።

26. Removal or Amendment of Entries from the Registry

1/ The Ministry shall have the power to remove or amend entries from the Register under the following circumstances:

a) upon the request of the legal person or its beneficial owner, provided that the request is supported by valid documentation;

b) if the information is found to be inaccurate or misleading after verification;

c) based on complaints submitted by persons with a legitimate interest;

d) based on the decision given by appropriate courts;

e) based on the motion of the Registry up on the identification of error up on filling out of the concerned information;

f) any unforeseen circumstances that require the amendment of the Information in the Registry.

2/ The Ministry shall request the concerned legal person to rectify the information, before proceeding with the amendment or removal process.

3/ The Ministry shall maintain a record of all removals and amendments, including the reasons for such actions.

፬/ ሚኒስቴሩ ስለተደረገው ለውጥ ለሚመለከተው በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል እና ወይም ተጠቃሚ ለሆነው ባለቤት በ፲ (ዓሥር) የስራ ቀናት ውስጥ ማሳወቅ አለበት።

፳፯. <u>መረጃን ስለማረጋገጥ</u>

፩/ ሚኒስቴሩ መረጃ ከተቀበለ በኋላ ምክንያታዊ እና መደበኛ በሆነ ሁኔታ የመረጃን በቂነት፣ ትክክለኛነት እና ወቅታዊነት የሚያሳይ የማረጋገጫ ሂደት ይዘረጋል።

፪/ የመረጃ ማረጋገጥ ሂደት ምንም ገደብ ሳይደረግበት ቢያንስ ከሌሎች መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆነ ዳታ ቤዝ ማጣሪያ ማድረግ፣ ቁጥጥር ማከናወን እንዲሁም ተጠቃሚ ከሚሆነው ባለቤት እና አግባብነት ካለው ሰው ተጨማሪ መረጃ እና ሰነድ መጠየቅን ያካትታል።

፳፰. <u>የመረጃ መጣረስ ማሳወቂያ ዘዴ</u>

፩/ ሚኒስቴሩ በመረጃ አሰባሰብ ሂደት የሚያጋጥምን የመረጃ አለመጣጣምና ትክክለኛ ያልሆነ መረጃን የሚያረጋግጥበትን ዘዴ መዘርጋት አለበት፡፡

፪/ የመረጃ መጣረስ የማሳወቂያ ዘዴዎች የሚከተሉትን ያካትታል፡-

ሀ) ስልጣን ያለው አካል ወይም ሰው የሚያቀርበው አስቸኳይ የመረጃ አለመጣጣምና ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ሪፖርት፤

4/ The Ministry shall notify any changes to the concerned legal person and or beneficial owner within 10 (Ten) working days.

27. <u>Verification of Information</u>

1/ The Ministry shall implement a verification process to ensure the adequacy, accuracy and up-to datedness of the information, within a reasonable time upon submission of the information, and on a regular basis thereafter.

2/ Verification may include, but is not limited to, cross-referencing with other governmental and non-governmental databases, conducting inspection, and requiring additional information and documentation from beneficial owners or other relevant persons.

28. <u>Discrepancy Reporting Mechanism</u>

1/ The Ministry shall establish a discrepancy reporting mechanism to address any inconsistencies or inaccuracies identified in the Information.

2/ Key points of the discrepancy reporting mechanism shall include:

a) prompt reporting of inconsistencies or inaccuracies by relevant authorities and persons;

ለ) ሚኒስቴሩ ሪፖርት የተደረገ የመረጃ አለመጣጣምና ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ላይ የሚያደርገው ምርመራ፤

ሐ) የተገኘ የመረጃ አለመጣጣምና ትክክለኛ ያልሆነ መረጃን እና የተወሰደ እርምጃ ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ።

፫/ የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ስራ ባለቤቶች ከደንበኛቸው ወይም በደንበኛ ልየታ ሂደት ወይም ከሌላ ታማኝ ምንጭ በሰበሰቡት መረጃ እና በሚኒስቴሩ በሚገኝ መረጃ መካከል የመረጃ አለመጣጣምና ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ መኖሩን ሲያረጋግጡ ይህንኑ መረጃ ለሚኒስቴሩ ማሳወቅ አለባቸው።

፬/ ከላይ የተመለከተው ማንኛውም የመረጃ አለመጣጣምና ትክክለኛ ያልሆነ መረጃን ያለምንም መዘግየት ሪፖርት መደረግ ያለበት ሲሆን በማንኛውም ሁኔታ የመረጃ አለመጣጣምና ትክክለኛ ያልሆነ መረጃው ከተለየ ጀምሮ በአስራ አራት የስራ ቀናት ውስጥ ሪፖርት መደረግ አለበት።

፭/ ሪፖርት በሚቀርብበት ወቅት የመረጃ አለመጣጣምና ትክክለኛ ያልሆነ መረጃን የሚያሳይ ደጋፊ ማስረጃ አባሪ መደረግ አለበት።

b) examination of reported inconsistencies or inaccuracies by the Ministry;

c) communication of findings and necessary corrective actions to relevant parties.

3/ Where Financial Institutions and Designated Non-Financial Business and Professions identify inconsistencies or inaccuracies between information held in the Ministry and the information they obtain from the customer or other reliable sources in the course of customer due diligence, they shall report those inconsistencies or inaccuracies to the Ministry.

4/ The inconsistencies or inaccuracies referred above shall be reported without undue delay and, in any case, within 14 working days of their detection.

5/ When reporting such inconsistencies or inaccuracies, it shall be accompany the reports with information they have obtained indicating the inconsistencies or inaccuracies.

ክፍል አራት

ተጠቃሚ የሆነ ባለቤት መረጃን ተደራሽ ስለማድረግ እና ማጋራት

፳፱. መርህ

ተጠቃሚ የሆነው ባለቤት መረጃን ተደራሽ የማድረግ እና የማጋራት ግልጸኝነት የግል መረጃ ከመጠበቅ መብት ጋር ሚዛናዊ መሆን አለበት።

፴. ተጠቃሚ የሆነው ባለቤት መረጃ ተደራሽነት

፩/ አግባብነት ያላቸው ባለስልጣናት ሙሉ፣ ቀጥተኛ እና ወቅታዊ የሆነ ተጠቃሚ የሆነ ባለቤት መረጃ ከሚኒስቴሩ ተደራሽ ይደረግላቸዋል።

፪/ በሚኒስቴሩ የተወሰነውን ክፍያ በመክፈል፣ የፋይናንስ ተቋማት እና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድ እና የሙያ ስራዎች፣ አግባብነት ባለው የጊዜ ገደብ ለተመዘገበ መረጃ ተደራሽ መሆን አለባቸው።

፴፩. ለሶስተኛ ወገኖች መረጃን ስለማጋራት

፩/ ህጋዊ ጥቅም ያለው መሆኑን በማስረጃ አስደግፎ ያቀረበ ማንኛውም ሰው በሚኒስቴሩ በወጣ መመሪያ የተወሰነውን ክፍያ በመክፈል መረጃ ማግኘት ይችላል።

፪/ ሚኒስቴሩ ህጋዊ ጥቅም ላላቸው ሰዎች የሚሰጥ እና የማይሰጥ መረጃ አይነት በመመሪያ መወሰን አለበት።

PART FOUR

ACCESSIBILITY AND SHARING OF INFORMATION

29. Principle

Accessibility and Sharing of Information shall balance transparency and the protection of personal data.

30. Access to Information

1/ Full, direct, and timely access to all information shall be granted to competent authorities by the Ministry.

2/ Financial Institutions and designated non-financial business and professions shall be granted an access to the information in timely manner, up on payment of fees to be determined by the Ministry.

31. Information Sharing to Third Parties

1/ Information held by the Ministry may be shared to any person who can demonstrate a legitimate interest in the information, upon the payment of the prescribed fee.

2/ The Ministry shall determine the types of information shared to persons with a legitimate interest.

፴፪. ልዩ ሁኔታዎች

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴ እና ፴፩ የተጠቀሰው የመረጃ ተደራሽነት ተጠቃሚ በሆነው ባለቤት ላይ የመጭበርበር፣ የመታገት፣ የማስፈራራት፣ የዝርፍያ፣ የትንኮሳ፣ የጥቃት ወይም የዛቻ ያልተመጣጠነ ስጋቶች የሚያጋልጥ ከሆነ ወይም ተጠቃሚ የሆነው ባለቤት አካለመጠን ያልደረሰ ወይም በሌላ አግባብ በህግ ችሎታ የሌለው ከሆነ ሚኒስቴሩ የመረጃውን ተደራሽነት በሙሉ ወይም በከፊል ሊያስቀረው ይችላል።

፪/ ሚኒስቴሩ የመረጃው ተደራሽነት መቅረት በጉዳዩ አይነት፣ ልዩ ሁኔታ እና የተጠቀሱት ያልተመጣጠኑ ስጋቶች መኖራቸውን በመገምገም መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

፴፫. የመረጃ ሚስጥራዊነት

በሚኒስቴሩ ወይም በሚመለከተው ሰው በጽሁፍ ካልተገለጸ በቀር፤ በዚህ ደንብ እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች መሰረት የተገኘ፣ የተሰበሰበ፣ የተቀመጠ፣ ሪፖርት የተደረገ፣ የተጋራ ወይም ይፋ የሆነ ማንኛውም መረጃ ሚስጥራዊነቱ የተጠበቀ መሆን አለበት።

32. Exceptions

1/ Where the access referred under Articles 30 and 31 would expose the beneficial owner to disproportionate risk of fraud, kidnapping, blackmail, extortion, harassment, violence or intimidation, or where the beneficial owner is a minor or otherwise legally incapable, the Ministry shall provide for an exemption from such access to all or part of the personal information on the beneficial owner.

2/ The Ministry shall ensure that such exemptions are granted on a case-by-case basis upon a detailed evaluation of the exceptional nature of the circumstances and confirmation that those disproportionate risks exist.

33. Confidentiality of Information

Any information obtained, gathered, stored, reported, shared or disclosed in accordance with this Regulation and other relevant laws shall be kept confidentially, unless expressly authorized by the concerned person or the Ministry, in written form.

ክፍል አምስት
ዓለም አቀፍ ትብብር

፴፬. መረጃ ማጋራት

ሚኒስቴሩ ከሌሎች አገራት መሰል የመንግስት ባለስልጣናት ጥያቄ ሲቀርብለት ወይም በራሱ ተነሳሽነት መረጃን ያጋራል።

፴፭. የመረጃ ጥያቄ

ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በውጭ አገር የተመዘገበ ወይም የሚገኝ የማንኛውም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካልን መረጃን መጠየቅ ይችላል።

፴፮. የድጋፍ ክትትል

ሚኒስቴሩ በጥያቄው መሰረት ከሌሎች አገራት የተቀበለውን ድጋፍ ጥራት መከታተል አለበት።

፴፯. የተመሳሳይ ተቋማት ትብብር

ሚኒስቴሩ ከሌሎች አገራት መሰል ተቋማት ጋር በቅንጅት እና ትብብር መስራት ይችላል፡፡

ክፍል ስድስት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፴፰. መረጃ የመጠየቅ እና የመቀበል ኃላፊነት

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን፣ የፋይናንስ ተቋም ያልሆኑ የንግድ ድርጅቶችና ሙያተኞች ፍቃድ ለሚሰጡትና የመቆጣጠር ስልጣን ባላቸው ህጋዊ አካላት ላይ መረጃ የመጠየቅና የመቀበል ኃላፊነት አለባቸው።

PART FIVE
INTERNATIONAL COOPERATION

34. Information Sharing

The Ministry shall share Information to other countries corresponding government authorities in its own initiative or up on request.

35. Request for Information

The ministry may request Information of any legal person residing or registered abroad from any country where it is found necessary.

36. Monitoring of Assistance

The ministry shall monitor the quality of assistance it has received from other countries in response to its request.

37. Cooperation with Similar Institutions

The ministry may work in coordination and cooperation with other jurisdictions Information registries.

PART SIX
MISCELLANEOUS PROVISIONS

38. Responsibility to Request and Obtain Information

National Bank of Ethiopia, Ethiopian Capital Market Authority, regulators of designated non-financial business and professions shall request and obtain Information from legal persons that they are authorized to license and supervise.

፴፱. እንቅስቃሴ የሌላቸው በህግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው አካላት

ሚኒስቴሩ እንቅስቃሴ የሌላቸውን በህግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው አካላት በመከታተል እና በመለየት ተመጣጣኝ እና የማያዳግም ቅጣቶችን መጣል፣ ዝርዝራቸውን በድረገጹ ላይ ለህዝብ ይፋ ማድረግ እና የንግድ ምዝገባ እና የንግድ ሥራ ፈቃዳቸውን መሰረዝ አለበት።

፵. አስተዳደራዊ ጥፋቶች

የሚከተሉት የሕግ ጥሰቶች አስተዳደራዊ ጥፋቶች ናቸው፡-

፩/ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ መረጃን አለማቅረብ፤

፪/ ያልተሟላ ወይም የተሳሳተ መረጃ ማቅረብ፤

፫/ የመረጃን ሚስጢራዊነት አለመጠበቅ፤

፬/ በ፲፬ የስራ ቀናት ውስጥ መረጃን አለማዘመን፤

፭/ ወቅታዊ የመረጃ ግምገማ አለማካሄድ እና ለሚመለከተው ባለስልጣን እንዲታይ አለማድረግ፤

፮/ የመረጃ ምዝገባ መኮንን አለመመደብ፤

፯/ በአዋጁ እና በዚህ ደንብ መሰረት መረጃን አለመያዝ፤

39. Dormant Legal Persons

The Ministry shall identify and trace dormant legal persons, impose proportionate and dissuasive sanctions, publicize the list of dormant legal persons on its website and revoke their commercial registration and business license.

40. Administrative Violations

The following legal violations constitute administrative violations:

1/ Failure to submit Information within the prescribed deadline;

2/ Submission of incomplete, Inaccurate or inadequate Information;

3/ Breach of the Confidentiality of Information;

4/ Failure to update Information within 14 days of any change;

5/ Failure to conduct periodic review of Information and made accessible to the concerned authority for consideration;

6/ Failure to assign Information registration officer;

7/ Failure to hold internal Information records as required by the Proclamation and this Regulation;

፰/ መረጃን ይፋ ለማድረግ እና ወይም ለማረጋገጥ ከሚመለከታቸው የባለስልጣን መስሪያ ቤቶች ጋር ለመተባበር ፈቃደኛ አለመሆን።

፵፩. አስተዳደራዊ ቅጣቶች

፩/ ሚኒስቴሩ የሚከተሉትን አስተዳደራዊ ቅጣቶች መጣል ይችላል፡-

ሀ) የዚህን ደንብ አንቀጽ ፵ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፪)፣ (፫) ወይም (፬) ድንጋጌዎችን ተላልፎ በተገኘ ሰው ላይ ከአንድ መቶ ሺህ ብር ያላነሰ እና ከአምስት መቶ ሺህ ብር ያልበለጠ የገንዘብ መቀጮ የመጣል፤

ለ) የዚህን ደንብ አንቀጽ ፵ ንዑስ አንቀጽ (፭) ወይም (፮) ድንጋጌዎችን ተላልፎ የተገኘን ሰው የንግድ ሥራ ፈቃድ የማገድ፤

ሐ) የዚህን ደንብ አንቀጽ ፵ ንዑስ አንቀጽ (፯) ወይም (፰) ድንጋጌዎችን ተላልፎ የተገኘን ሰው የንግድ ምዝገባ የመሰረዝ።

8/ Refusal to cooperate with competent authorities in disclosure and or verification of Information.

41. Administrative Sanctions

1/ The Ministry may impose the following administrative sanctions:

a) fines not less than One Hundred Thousand and not more than Five Hundred Thousand Birr shall be imposed on any person who violates Article 40 Sub Article (1) (2), (3) or (4) of this Regulation;

b) suspension or revocation of a business license shall be imposed if a person violates Article 40 Sub Article (5) or (6) of this Regulation;

c) the business registration shall be cancelled if a person violates Article 40 Sub Article (7) or (8) of this Regulation.

፪/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከሚጥለው ቅጣት በተጨማሪ የተቀጣው ሰው በህግ ተገገር እስከሚሆን ድረስ ከመንግስት የግዥ ስርዓት ወይም ከማንኛውም የመንግስት ድጋፍ በጊዚያዊነት እንዲታገድ ወይም ሙሉ በሙሉ እንዲገለል ለፌደራል የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ባለሥልጣን ማሳወቅ እና የተቀጣውን ሰው ስም በሚኒስቴሩ ኦፊሴላዊ ጋዜጣ ወይም ድረ ገጽ ላይ እንዲታተም ማድረግ ይችላል።

፵፪. <u>ቅሬታ ስለማቅረብ</u>

በዚህ ደንብ መሠረት በተጣለ አስተዳደራዊ ቅጣት ላይ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ውሳኔው በደረሰው በአስራ አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ በፌደራል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹፫/፪ሺ፲፪ ድንጋጌዎች መሠረት ቅሬታውን ለሚኒስቴሩ ማቅረብ ይችላል።

፵፫. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>

፩/ ነባር የህግ ሰውነት ያላቸው አካላት ይህ ደንብ ከጸናበት ቀን ጀምሮ መረጃቸውን፡-

ሀ) በ፫ ወራት ጊዜ ውስጥ መቀበል እና መያዝ፤ እና

ለ) በ፮ ወራት ጊዜ ውስጥ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ፤ አለባቸው።

፪/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን የጊዜ ገደብ እስከ ሁለት ወራት ጊዜ ሊያራዝም ይችላል።

2/ The Ministry may impose Temporary Restriction or exclusion from any public procurement or government support until compliance and notify same to the Federal Public Procurement Service and publicize names of sanctioned entities in its official gazette or website in addition to the sanctions specified in Sub Article (1) of this Article.

42. <u>Grievance Handling</u>

Any person who is aggrieved by an administrative sanction imposed in accordance with this Regulations may lodge his complaint in writing to the Ministry within Fifteen working days from the receipt of such decision pursuant to the provisions of the Federal Administrative Procedure Proclamation No. 1183/2020.

43. <u>Transitional Provisions</u>

1/ Existing legal persons shall, after the effective date of this Regulation:

a) obtain and hold their information within 3 months; and

b) submit their information to the Ministry within 6 months.

2/ The Ministry may extend the deadline stipulated under Sub Article (1) of this Article for not more than Two months.

፵፬. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፫ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም

አብይ አህመድ (ዶ/ር)

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

44. Effective Date

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, On this 10th Day of July, 2026

ABIY AHMED (Dr.)

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA